የ2016 ዓ.ም የአንደኛ መንፈቅ ዓመት በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 ትምህርት ፅ/ቤት የካራ ቆሬ ክላስተር ማዕከል የ6ኛ ክፍል የግብረ-ገብ ሞዴል ፈተና

የጥያቄ ብዛት: 40

የተፈቀደው ሰዓት: - 1 ሰዓት

አጠቃላይ ትዕዛዝ

ይህ የግብረ-ገብ ፈተና ነው፡፡ በዚህ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ እያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል፡፡ በፈተና ላይ የተሰጡትን ትዕዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል፡፡ መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው ፤ በመልስ "መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛው መልስ በማጥቆር ሲሰራ ማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መፅዳት አለበት፡፡ ፈተናውን ሰርቶ ለመጨርስ የተፈቀደው ሰአት 1 ሰአት ነው፡፡ ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናውን መስራት ማቆም አለብን፡፡ ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን፡፡

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰአት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል፡፡

ፈተናውን መስራት ከመጀመራቹሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት ሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት፡፡

ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !

1. የግብረ ገብ ምሉዕነት አለመኖር የሚያስከትለው ችግር ያለሆነው የቱ ነው
   ሀ. መስረቅ ሐ. ማጭበርበር
   ለ. ሀቀኝነት መ. መስና
2. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የግብረ ገብ ምሉዕነት መላበስ የሚያመጣው ጥቅም ነው
   ሀ. የሌሎችን ክብር ማግኘት ሐ. ተቀባይነት ማጣት
   ለ. መዋሸት መ. ጓደኛ አልባ መሆን
3. -------- ማለት ለሌሎች መታዘዝ ማለት ነው
   ሀ. ትህትና ሐ. ግትርነት
   ለ. ድፍረት መ. እምነትን ማጉደል
4. የግብረ ገብ ምሉዕነት መጓደል የሚታይባቸው ሰዎች ከሚከተሉት ባህሪያት ውስጥ አንዱ ይታይባቸዋል
   ሀ. ከፍ ያለ በራስ የመተማመን ብቃት አላቸው ሐ. ዝቅተኛ በራስ የመተማመን ዝንባሌ አላቸው
   ለ. ለሌሎች ክብር ይሰጣሉ መ. ሚስጥር ይጠብቃሉ
5. ውጤቱ ምንም ይሁን ምንም እውነትን ብቻ የመናገር ብቃት -------ይባላል
   ሀ. ወጥነት ሐ. ተለዋዋጭነት
   ለ. ሀቀኝነት መ. አስመሳይነት
6. ----------- ማለት አንድ ሰው ትክክል ነው ብሎ የሚያምንበትን ነገር እንዲተገበር የሚያደርግ ውስጣዊ ችሎታ ነው
   ሀ. ግልፀኝነት ሐ. ድፍረት
   ለ. ሚስጥር ጠባቂነት መ. ኢ-ተለዋዋጭነት
7. ------------ ማለት በግላችን ለምንወስዳቸው ውሳኔዎች ውጤቱ ጥሩም ይሁን መጥፎ ዝግጁ ሆኖ መቀበል ነው
   ሀ. ሀቀኝነት ሐ. ለራስ ክብር መስጠት
   ለ. ሀላፊነት መውሰድ መ. ትህትና
8. ከሚከተሉት ውስጥ የግብረ ገብ ምሉዕነት መገለጫ ያልሆነው የቱ ነው
   ሀ. ኢ-ተለዋዋጭነት ሐ. ትሁት መሆን
   ለ. ሚስጥር ጠባቂነት መ. መዋሸት
9. ከሚከተሉት አንዱ እውነተኛ የግብረ-ገብ ምሉዕነት የተላበሰ ሰው ባህሪ አይደለም
   ሀ. በማህበረሰቡ ውስጥ ታማኝነት የላቸውም ሐ. ሰዎችን ያከብራሉ
   ለ. ሀቀኛ ናቸው መ. ትሁት ናቸው
10. የሰውን አካል እና አዕምሮ የሚጎዳ በሽታ ነው
    ሀ. ሰላምን መጠበቅ ሐ. አደንዛዥ እፅ
    ለ. የፍትህ መኖር መ. የሰውነት እንቅስቃሴ

11.------------ማለት እራስን በሌሎች ቦታ በማድረግ ስለነሱ በማሰብ ስሜታቸውን መረዳት ማለት ነው

ሀ. ድፍረት ሐ. ሀቀኝነት

ለ. ወጥነት መ. ስለሌሎች ማሰብ

12.ከሚከተሉት ውስጥ በግብረ-ገብ ምሉዕነት ራሳቸውን የሚመሩ ሰዎች ባህሪ አይደለም

ሀ. በራስ መተማመን አላቸው ሐ. ሚስጥር ጠባቂ ናቸው

ለ. አስመሳይ ናቸው መ. ታጋሽ ናቸው

13.ከሚከተሉት መካከል በትምህርት ቤት ደረጃ የግብረ-ገብ መገለጫ የሆነው የቱ ነው

ሀ. ፈተናን አለመኮረጅ ሐ. የደንብ ልብስ ለብሶ መገኘት

ለ. አለማርፈድ መ. የት/ቤት ንብረትን ማበላሸት

14.እውነተኛ የግብረ-ገብ ምሉዕነት የተላበሰ ሰው ከሚከተሉት አንዱ ባህሪ ሊኖረው አይገባም

ሀ. ድፍረት ሐ. ኢ-ተለዋዋጭነት

ለ. ሀላፊነትን መውሰድ መ. ሀቀኝነት የጎደለው

15.----------ስልጣን ባላቸው ግለሰቦች የሚፈፀም የወንጀል ባህሪ ነው

ሀ. ሙስና ሐ. ፍትህ

ለ. ነፃነት መ. ግብር ስወራ

16.ህጻናትን ለተለያዩ ስራዎች እና ለወሲብ ተግባራት የማሰማራት ሂደት ነው

ሀ. የሰላም እጦት ሐ. የፍትህ እጦት

ለ. ህገ-ወጥ የህጻናት ዝውውር መ. ማጭበርበር

17.ከሚከተሉት መካከል ሙስና መገለጫ የሆነው የቱ ነው

ሀ. የዝምድናና ወገንተኝነት አሰራር ሐ. ጉቦ መስጠት

ለ. ማጭበርበር መ. ሁሉም መልስ ናቸው

18.ከሚከተሉት ውስጥ ለህግ ተገዥ አለመሆን የሚያስከትለው ውጤት ያልሆነው የቱ ነው

ሀ. የነፃነት እጦት ሐ. የሰበአዊ ሙብት ጥሰት

ለ. ሙስና መ. የፍትህ መስፈን

19.መልካም ባህሪን ለማሳደግ የሚያስችለው ከሚከተሉት ውስጥ የቱ ነው

ሀ. ራስን መቆጣጠር ሐ. ራስ ወዳድነት

ለ. ህግና ደንብን አለማክበር መ. ለራስ ብቻ ክብር መስጠት

20.ከአደንዛዥ እፅ ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው

ሀ. ሲጋራ ሐ. ጫት

ለ. ለስላሳ መ. ሺሻ

21.----------ማለት የራስና ጥቅም ማስቀደም እና ስለሌሎች ጥቅም አለመጨነቅ ማለት ነው

ሀ. ፍትሀዊነት ሐ. የግል ፍላጎትን ማስቀደም

ለ. ታማኝነት መ. ክብር መስጠት

22.ህፃናትን በህገ-ወጥ መንገድ ከሚዘዋወሩባቸው ምክንያቶች መካከል የማይጠቀሰው የቱ ነው

ሀ. ለሴት አዳሪነት ሐ. ለልመና

ለ. ለተለያየ የጉልበት ስራ መ. የተሻለ ሂወት ለመስጠት

23.ከሚከተሉት መካከል አንዱ ከህግ ባህሪያት ውስጥ አይመደብም

ሀ. ቋሚነት ሐ. የፍትህ እጦት

ለ. ተለዋዋጭነት መ. ወጥነት

24.------------ ማለት ግጭት ያለመኖር ማለት አይደለም

ሀ. ሰላም ሐ. ታማኝነት

ለ. ነፃነት መ. ሀቀኝነት

25.ከሚከተሉት ውስጥ ግብርን ላለመክፈል የሚደረግ ህገወጥ ሙከራ ውስጥ አይካተትም

ሀ. ወጭን ማጋነን ሐ. ገቢን ማሳነስ

ለ. ግብርን በወቅቱ መክፈል መ. ሰነድን መደበቅ

26.----------- ያልተገባ ጥቅምን ለማግኘት ለባለስልጣን ገንዘብ መስጠት ማለት ነው

ሀ. ማጭበርበር ሐ. ጉቦ መስጠት

ለ. ዝምድና ና ወገንተኝነት መ. ግብር ስወራ

27. ሕገ-ወጥ የህፃናት ዝውውርን መዋጋት እና መታገል ያለበት ማን ነው

ሀ. መንግስት ሐ. ማህበረሰቡ

ለ. ፖሊስ መ. ሁሉም

28.ለህግ ተገዥ የሆነ ሰው ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው

ሀ. መብት እና ግዴታቸውን ያውቃሉ ሐ. ሃላፊነታቸውን በአግባቡ ይወጣሉ

ለ. በሰዎች ዘንድ እምነት አይጣልባቸውም መ. ታማኝ ናቸው

29.----------- ማለት ውስጣዊ ስሜትን መቆጣጠር (ማቀብ) ማለት ነው

ሀ. ራስን መቆጣጠር ሐ. ባህሪ

ለ. ዋጋ መ. ሚስጥር ጠባቂነት

30.ከሚከተሉት ውስጥ ጥሩ ባህሪ ያለው ሰው መለያ ያልሆነው የቱ ነው

ሀ. ለሰዎች ክብር መስጠት ሐ. እንግዳ ተቀባይነት

ለ. የገባውን ቃል ማክበር መ. ሌሎችን አለማክበር

31.ከሚከተሉት ውስጥ የሁሉም ኢትዮጵያን የግብረ-ገብ እሴት የሆነው የቱ ነው

ሀ. ለአረጋውያን ክብር መስጠት ሐ. ወላጆችን ማክበር

ለ. መምህራንን ማከብር መ. ሁሉም መልስ ናቸው

32.ክብር የሚጀምረው ከየት ነው

ሀ. ከራስ ሐ. ከጎረቤት

ለ. ከጓደኛ መ. ከአካባቢ

33.መልካም ባህሪን አለመላበስ የሚያስከትለው ውጤት ያልሆነው የትኛው ነው

ሀ. በራስ መተማመን ሐ. በሰዎች ዘንድ ክብር ማግኘት

ለ. የእርስ በእርስ ግጭት መ. ሃላፊነት መውሰድ

34.ከሚከተሉት መካከል ለአካባቢ ክብር መስጠት ሲባል ምን ማለት ነው

ሀ. ቆሻሻን በየቦታው መጣለል ሐ. ዛፎችን መትከል እና መንከባከብ

ለ. መንገድ ላይ መሽናት መ. የአካባቢ ንፅህናን አለመጠበቅ

35.--------- ማለት ድርጊቶችን እና ውሳኔዎችን በእምነት መምራት መቻል ማለት ነው

ሀ. ሀቀኝነት ሐ. ራስን መቆጣጠር

ለ. ታማኝነት መ. ተጠያቂነት

36.ከሚከተሉት መካከል የሀቀኛ ሰው መለያ ያልሆነው የቱ ነው

ሀ. ከጓደኞቹ ጋር ውጤታማ ተግባቦት መኖር ሐ. በራስ አለመተማመን

ለ. ፍቅር እና ሞገስ መግኘት መ. ለራስ ዋጋ መስጠት

37.የመልካም ባህሪ ምሳሌዎች የሆነው የትኛው ነው

ሀ. ትሁት አለመሆን ሐ. በራስ አለመተማመን

ለ. ለሰሩት ስህተት ይቅርታ መጠየቅ መ. ሁሉም

38.መልካም ባህሪ ከሚከተሉት ውስጥ የየትኞቹ ድምር ውጤት ነው

ሀ. የቤተሰብ ሐ. የምርጫ

ለ. የጊዜ መ. ሁሉም

39.እውነተኛ የግብረ ገብ ምሉዕነት የተላበሰ ሰው ከሚከተሉት አንዱ ባህሪ ሊኖረው አይገባም

ሀ. ሀቀኝነት የጎደለው ሐ. ወጥነት

ለ. ድፍረት መ. ሀላፊነት መስጠት

40.ከሚከተሉት መካከል የግብረ ገብ ምሉዕነት መገለጫ ድርጊት ነው

ሀ. ሀቀኛ መሆን ሐ. አለመታመን

ለ. እውነትን መናገር መ. ሀ እና ለ

በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 ት/ጽ/ቤት የካራ ቆሬ ክላስተር ማዕከል የ6ኛ ክፍል ግብረ-ገብ ሞዴል ፈተና

ታህሳስ/2016